# የACPS Express 11/11/2022: የACPS PTAs፣ የቤተሰብ ተሣትፎን ያበረታታሉ

## የኖቬምበር (November) - በአጋርነት እና በነ-ፍቃደኝነት (Partner & Volunteer) ላይ የሚታዩ-ጉልህ ነገሮች: የACPS PTAs፣ የቤተሰብ ተሣትፎን ያበረታታሉ



የወላጅ-አስተማሪ ማኅበር (Parent Teacher Association (PTAs)፣ ከአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ጋር ቁርኝት-ያለው እና፤ በክፍሉ/division ውስጥ - የቤተሰብ ተሣትፎ ስራን በማከናወን ይረዳል። በዚህ ወር፤ የትምህርት ቤታችንን ‘PTAs’ እና የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (PTAC) - ከቤተሰቦች ጋር እንዴት እንደሚሳተፉ በማጋራታቸው ላይ በጉልህ-የምንመለከትበት ወር ነው።

”ተማሪዎቻችንን የከበቡት ጠቅላላ-ማህበረሰቡ ያላቸውን ተሰጥዖዎች፣ ጊዜ እና ሌላ የመረጃ-ምንጭን በሚሰጡ-ጊዜ፤ ትምህርት ቤቱ ወደፊት በመራመድ የሚመለጽግበት ግሩም-ዕድል አለው፤” ብለዋል፣ በቻልስ ባሬት (Charles Barrett) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት - የ‘PTA’ ፕሬዚዳንት የሆኑት - ሴራ መርቻዶ ማቲውስ (Sara Mercado Mathews)። በመጨመርም-ሲናገሩ፤ የማህበረሰብ እርዳታ-በሁለቱም መንገዶች ይረዳል፤ “የፒቲኤ (PTA) የሚጠቀምበት የሚስጥር-ቅመሙ ያ-ይመስለኛል — ሁልጊዜ ከሰጣችሁት በላይ ታገኛላችሁ።”

የላየልስ-ክራውች ትራድሽናል አካዳሚ (Lyles-Crouch Traditional Academy  (LCTA) የ‘PTA’ ፕሬዚዳንት - ማቲአስ ፓአላቬንቺኖ (Matias Palavecino)፤ ፒቲኤ (PTA)ን የሚመለከቱት - እንደ ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር ትውውቅን-መፍጠሪያ መንገድ አድርገው ነው። “ከማህበረሰብ-አባላቶቻችን ጋር አብሮ-መሆንን ሁልጊዜ እንወዳለን፤ እና አዲስ ጓደኞችን ማግኘት እና ከመማሪያ-ክፍሎች እና የክፍል-ደረጃዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ ደስ-ይለናል።” ጨምሮ-ሲገልጹም፤ የ‘LCTA PTA’ ሣምንታዊ ኢሜል - ስለ ትምህርት ቤት ዜናዎች እና ቁልፍ-የሆኑ የACPS መልዕክቶችን የሚያስተጋባበት ነው። በስራ-ላይ የዋለው የኦንላይን የወላጆች የቡድን መረጃዎችን መጋሪያ፣ ጥያቄዎችን መልስ ማግኛ፣ እና ስብጥር-ያላቸውን አመለካከቶች የሚቀበልበት ነው።








“ቤተሰቦች በሚሳተፉ ጊዜ፣ ልጆቻቸው ምን ትተሞክሮ-እንዳላቸው በተሻለ-ሁኔታ የሚረዱበት፣ እና አስተማሪዎቻቸው ለመማር ፍላጎታቸውን የሚያገኙበት፣ እና በመኖሪያ ቤት ውስጥ ልጆቻቸውን ለመርዳት መንገዶችን በመፈለግ - በትምህርት ቤት ውስጥ የተካሄደውን

የሚያጠናክሩበት ነው፣” በማለት-አብራርተዋል ማሪና ካርተር (Marina Carter) - የማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት - (MVCS)፣ የPTA ፕሬዚዳንት። ካርተር (Carter)፤ የትምህርት ቤት ፒቲኤ (PTA)ውን እንደ “ለትምህርት ቤታችን እና ቤተሰቦች እንደ ድልድይ ሆኖ፤ ለልጆች ሁሉን ተቀባይነት-ባለው አካባቢ - የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸው እርዳታ-የሚሰጣቸውን መንደርን መፍጠር ነው።”

የጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት (Jefferson-Houston)፣ የፒቲኤ (PTA) ፕሬዚዳንት የሆኑት ናታሊ ክሊዌል (Natalie Clewell) እንዳሉት፤ የቤተሰብ ተሣትፎ ትኩረት የሚያደርገው በማህበረሰብ፣ በተማሪዎች/ቤተሰቦች እና ተከራካሪ-ወኪል (advocacy) በመሆን ላይ ነው። “ቤተሰቦች፤ በማንኛውም ዓይነት መንገድ፣ እነርሱ እንደሚፈልጉት እና እስከሚፈልጉበት ደረጃ ደረስ፤ በማንኛውን-ዓይነት መንገዶች ለእነርሱ በተመቻቸላቸው ሁኔታ ለመሣተፍ እንዲችሉ-ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፤” ክሊዌል (Clewell) ሲያብራሩ። አንዳንድ ቤተሰቦች - እንቅስቃሴዎችን በአንድነት-ለማድረግ እርዳታ-ሲያደርጉ፤ ሌሎች ደግሞ ተወካይ ተከራካሪ  ሆኖ ለአስተማሪዎች እና ለተማሪዎች በክፍል/division አመራርነት ውስጥ መሳተፍን ይመርጣሉ።

የቤተሰብ ተሣትፎ፤ እያንዳንዱ-ልጅ በትምህርታቸው ላይ እና በህይወት ጉዞአቸው ላይ እርዳታን-ማግኘታቸውን ማረጋገጫ ቁልፍ-የሆነ አካል-ነው። እንዲዚህ-ነው፣ የዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት - የፒቲኤ (PTA) ፕሬዚዳንት - የሆኑት መታ ቪየርስ (Meta Viers) - የሚመለከቱት። “በተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና በአስተማሪዎች መካከል ያለው ጠንካራ ግንኙነቶች፤ በአብዛኛው-እንደሚያሳየው - ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ እና የመረጃ-ምንጮች - በመማሪያ-ክፍል ውስጥ እና ውጪ ለማግኘት-ያስችላቸዋል፤” በማለት አስታውሰዋል - ቪየርስ (Viers)። በተጨማሪም፤ የቤተሰብ ተሣትፎ መኖር፤ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በበለጠ ደስተኛነት፣ በመደበኛነት እና በበለጠ በቀለም-ትምህርት ጥሩ ለመስራት ተበረታችነትን ያስገኛቸዋልም - ብለው ያምናሉ።

የኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት፤ ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂ (Math, Science and Technology’s (Cora Kelly) ፒቲኤ (PTA)፤ የበለጸገ የተማሪ ተሞክሮን ለማቅረብ-እንዲቻል - ቤተሰቦችን ከትምህርት ቤት ሠራተኞች እና አስተዳደር ጋር አቅርቦ-በአንድነት ማምጣት ትልቅ-ዋጋ እንዳለው አስምሮበታል። ቦኒ ናውጌል (Bonnie Naugle)፣ የኮራ ኬሊ/Cora Kelly) ፒቲኤ (PTA) ቃል-አቀባይ የሆኑት ሲናገሩ፤ ሁሉም ቤተሰቦች ለመቀላቀል የሚችሉ እና ትምህርት ቤትን፣ አስተማሪዎቹን፣ እና ተማሪዎችን፤ የሚያግዙ ዝግጅቶችን ለማቀድ እና ሚናን-ለመጫወት መሳተፍ-ይችላሉ። እርሳቸውም-በመቀጠል ሲገልጹ፤ ባለፈው-ዓመት በነበረው የCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት፤ ለምሳሌ - ትምህርት ቤቶች ለቤተሰቦች እንዲያከፋፍሉ 100 የሙቀት-መለኪያ ቴርሞሜትሮች (thermometers) ፒቲኤ (PTA) በመለገስ፤ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ከማምጣታቸው በፊት የሰውነት-ሙቀታቸውን መለካት ለሚያስፈልጋቸው ወላጆች፤ አከፋፍሏል።

የቤተሰብ ተሣትፎ - በበርካታ ዓይነት ሁኔታዎ ይመጣሉ፤ ገንዘብ-አሰባሳቢዎች (fundraisers)ን ከመርዳት - እስከ በአስደሳች ሩጫ ውስጥ እና በሌሎች ዝግጅቶች ውስጥ በ18ቱን የACPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ መካፈልን ያካትታል። የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የወላጅ አስተማሪ ተማሪ ማኅበር (Parent Teacher Student Association (PTSA) - ፕሬዚዳንት የሆኑት ኬቲ ማቲውስ (Katy Matthews) ሲናገሩ፤ “እኔ የበጎ-ፈቃደኝነት ስራውን የወሰድኩት - የACPS አስተማሪዎች የትምህርት አሰጣጥ የፕሮግራም የመረጃ-ምንጮችን በ‘PTSA’ የገንዘብ-እርዳታዎች አማካኝነት፤ መክሰሶች (snacks)ን በማራቶን የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች ወቅት፣ በ‘school’s Positive Behavior Interventions and Supports (PBIS)‘ የፕሮግራም አሰጣጥ - ሽልማቶችን - የውጪው-አለም ምንም-እርዳታ እንደማይሰጥ ሆኖ በሚሰማቸው ጊዜ ለመርዳት ነው።” የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (GWMS) የፒቲኤ (PTA) ፕሬዚዳንት የሆኑት ጆይ ፓስቻቲላ (Joy Pochatila) በንግግራቸው-ላይ፤ “የእኛ ‘GWMS’ ሠራተኞች - ቤተሰቦቻችን ምን እንደሚፈልጉ ትርታቸውን በማዳመጥ-ላይ ጥሩ ጣቶች-አሏቸው፣ እና ጥረታቸውንም በመደገፍ - ፒቲኤ (PTA) ምላሽ-የሰጣቸዋል።”





የ‘PTAC’ ፕሬዚዳንት - ሚሲ ሳንቶሮ እስታብሩክ (Missy Santoro Estabrook)፤ በቤተሰብ ተሳትፎ ዝግጅቶች ላይ በቅርበት አጋር ከሆኑ ትምህርት ቤቶች - ፒቲኤ (PTAs) ይኮራባቸዋል። ሳንቶሮ ኢስታብሩክ (Santoro Estabrook) እንዳሉት፤ ይህ የእያንዳንዱ የ‘PTA’ ክፍያ ለመቀነስ-ብቻ ሣይሆን፣ ነገር ግን ከአጎራባቾች ጋር ግንኙነት ለመፍጠርም የሚረዳ-ነው፤ ብለዋል። “ለቤተሰቦቻችን ወኪል-ተከራካሪ በምንሆን-ጊዜ ቅንጅትን መገንባቱ  - ከዚያ የበለጠ ምንም-ዋጋ የሚሰጠው የለም፤” ብለው-አስታውሰዋል። ባለፈው ፀደይ (spring) ወቅት፤ ፒቲኤ (PTAs) ከሦስት ትምህርት ቤቶች — ጄምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (Polk)፣ ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት እና ዳግለስ ማክአርተር (Douglas MacArthur) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (MacArthur) — አስደሳች-የሆነ ሩጫን ለማዘጋጀት-አብረው በትብብር-ሰርተዋል። የ‘ፖልክ (Polk)’ እና ‘ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry)’ ፒቲኤስ (PTAs)፤ የፊልም ምሽትን በጋራ-ያዘጋጃሉ። የፖልክ (Polk) የፒቲኤ (PTA) ፕሬዚዳንት - ቻአሮን ፒርሰን (Chaaron Pearson)፤ በፖልክ (Polk) ሕዝብ-ውስጥ ያለው ስብጥር-በጣም የሰፋ እንደሆነ እና የቤተሰብ ተሣትፎ የ‘PTA’ ዋናው እሴቱ እንደሆነ ተናግረዋል። “አብሮ-መብላት እና በአንድ-ላይ ሆኖ የመማር ዕድል ባለበት ቦታ ላይ፣ ቤተሰቦችን ከትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ጋር በደስተኛነት በማቀራረብ፤ የበለጠ-ስኬትን አግኝተናል፤” ብለው ጨምረውበታል። የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ፒቲኤ (PTA) መሪ - ጄኒካ ፓተርሰን (Jenica Patterson)፤ እነዚህ ዝግጅቶች፣ ቤተሰቦችን በአንድነት-እንዲሰሩ እና እንዲጫወቱ ለማምጣት-ወሳኝ-የሆኑ ዝግጅቶች መሆናቸው እንደሚሰማቸው ተናግረዋል።

በአካል-ተገኝቶ (in-person) ዝግጅቶች በCOVID-19 ምክንያት መቋረጣቸውን-በተከተለ ሁኔታ፤ አሁን - ፒቲኤ (PTAs) በአካል-ተገኝቶ ሁሉን በማገናኘት እና ለአስተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ያላቸውን-ምስጋና በማቅረብ-ላይ ትኩረት አድርገዋል። አንዳንድ፣ ስናፕሻቶች (snapshots) የሚያካትቱት:

- የ‘LCTA’ ዓለም-አቀፍ ምሽት፤ የማህበረሰቡን ሰፊ-የሆነ ስብጥርን በጉልህ-የሚያሳይ ነው። “እነዚህ ዝግጅቶች፣ ማህበረሰባችን በአንድነት-ሁሉ እርስ-በራሱ ለመረዳዳት ሲመጣ እንዴት ጠንካራ-መሆን እንደሚቻል ለማሳየት የቻለ እና እንደማህበረሰብ-አብሮ የመሆን ጊዜያችንን እየተደሰትንበት መሆኑን ያሳያል፤” ብለዋል ፓላቬቺኖ (Palavecino)።
- ኮራ ኬሊ (Cora Kelly) - የፒቲኤ (PTA) - ‘Harvest Festival’ን በተሳካ-ሁኔታ ያከናወነ እና፣ ከACHS ጋር እንዴት-ሃይሉትን እንዳጠናከረ፣ የተማሪ የበጎ-ፈቃድ-ሠራተኞችን ለእርዳታ - በቡቶች (booths) እና በእንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲረዱ በመቅጠር - ስኬት-አስመዝግቧል።
- ቻርልስ ባሬት (Charles Barrett) ፒቲኤ (PTA)፤ ለቤተሰቦች ሁሉን-ተቀባይ የሆነ አካባቢን በመፍጠር እና በ“Boo Hoo Breakfast” አማካኝነት - የተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ቀን የማውረጃ (drop-off) ተከትሎ በማካሄድ፤ የማህበረሰብ-ግንኙነቶችን አዳብሯል።
- የቢንጎ-ምሽት (Bingo Night) - በዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) ውስጥ የበልግ (fall) ጉልህ-ክንውኑ የሆነ እና፣ ማህበረሰቡን በአንድነት-አብሮ ለማምጣት የሚረዳ ነው። ቪየርስ (Viers) እንዳሉት-ከሆነ፤ ፒቲኤ (PTA) - የ‘spirit wear’ ሱቅን - በዚህ ዓመት - ገንዘብን-ለማሰባሰብ እና ሁሉን-በጋራ የሚያሳትፍ መማርን ለመደገፍ-እንዲያስችል፤ አዘጋጅቷል።
- የፈርድፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (FTD) - ፒቲኤ (PTA) ያዘጋጀው፤ የአርት አውደጥናት (art workshop)-የአይስ ክሬም የማህበራዊነት ከታሪክ ማንበቢያ ጊዜ ጋር በማዘጋጀት፤ የ‘PTA’ ፕሬዚዳንት አሊኦኔ ዲአሎ (Alioune Diallo) - ለበርካታ የFTD ትእማሪዎች - “ህልም እውን-ሆነ” ብለው-ጠርተውታል። “በዚህ ዓመት አንዱ-ግባችን - ተማሪዎቻችንን ለማገዝ - በተለይ-ደግሞ በእንግሊዘኛ-ቋንቋ ለሚቸገሩ፣ በቤተሰብ ተሣትፎ አማካኝነት የቋንቋ ችሎታዎችን ለማሻሻል - ይህን በማድረግም፣ ሁሉንም ፈተናዎቻቸውን በስኬት ለማለፍ፣ የትምህርት

ዓመታቸውን ለማጠናቀቅ፣ እና፣ በአምስተኛ ክፍል ውስጥ ላሉት-ወደ ሚቀጥለው ክፍል በዓመቱ-መጨረሻ ላይ ለመሸጋገር የሚያስችላቸው ይሆናል፤ ብለዋል ዲአሎ (Diallo)።






ምርምር (Research) እንደሚያሳየው ከሆነ፤ የቤተሰብ ተሣትፎ ያለበት ጨዋታዎች - በተማሪዎች ስኬት ላይ ጉልህ-የሆነ ሚናን እንደሚጫወት-ያሳያል። “ቤተሰቦቻቸው የሚሣተፉ - ተማሪዎች፤ በአብዛኛው - በትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው የሚማሩ፣ የስነ-ምግባት ችግሮችን የሚያስወግዱ፣ በቀለም-ትምህርታቸው የላቀ-ደረጃ የሚያገኙ እና በጊዜው-የሚመረቁ ናቸው፣” ብለዋል-አስታውሰዋል፤ ሳንቶሮ እስታብሩክ (Santoro Estabrook)። የ‘PTAC’ ፕሬዚዳንት በመጨመርም፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ ፒቲኤ (PTA) አመራር፣ ለብቻው-ወደተዘጋጀለት ዕቅድ፣ የየግል-እና ከበካታ-ግሩም ሃሳቦች ያሏቸው ፕሮግራሞች ጋር በመሆን-ስብጥር ያላቸው አስተሳሰቦችን ከሚያቅፉት ጋር በመሆን፤ የእያንዳንዱን ልጅ ልዩ የሆኑ ፍላጎቶችን ከማሟላት ጋር እና በትምህርት ቤት እና በመኖሪያ-ቤት ህይወታቸው መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠንከር፤ ወደ ብልጽግና-ጎዳና ይጓዛል። “የእኛ ፒቲኤ (PTAs) በዚህ ዓመት - ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ፍላጎቶች መሟላት ተጠሪ-ተከራካሪ ለመሆን ጉልበት-እንዲኖራቸው በማድረግ እና ሁሉም የቤተሰብ ተሣትፎ ዝግጅቶች እና ፕሮግራሞች - ለልጆቻችን ደስታን-ለማምጣት እና አቅማችውን እውን-ለማድረግ በመርዳት ላይ ሁሉም ትኩረት በማድረጋቸው - በእነዚህ በተደረጉት ነገሮች ሁሉ - በእውነት ኮርቻለሁ፤” ብለዋል ሳንቶሮ እስታብሩክ (Santoro Estabrook)።

‘PTAs’ ነገሮችን-ሊቀይር ወደሚችል የቤተሰብ ተሣትፎ መንገዱን እንዴት እንደሚመራ -ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ ‘The Center for Family Engagement | National PTA’ን ተመልከቱ፤ እና ስለአካባቢያችሁ ‘PTA’፣ በትምህርት ቤታችሁ ድህረ-ገጽ ላይ ወይም በ‘PTAC’ ድህረ-ገጽ ላይ አግኙ።

## ACPS፣ የ2022- 23 የመጀመሪያ የ‘VIP’ ሽልማት አሸናፊዎችን አስታወቀ





የመጀመሪያው የ‘Vision, Integrity and Passion (VIP)’ ተቀጣሪ - ለ2022-23 የትምህርት ዓመት የተመረጠ-የነበረ እና እውቅናን-አግኝተው ተሸልመዋል። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ በመጓጓዣ፣ በአመጋገብ አገልግሎቶች፣ እና በህንፃ ምህንድስና ምድቦች፤ የሚከተሉትን አሸናፊዎች አስታውቃል:

- ሞንያ ባልድዊን (Monya Baldwin)፣ የACPS በልዩ-ሁኔታ የሚሰጥ መጓጓዣ (specialized transportation) አስተባባሪ - ከACPS ከ2018 ጀምሮ የነበሩ።

- ሎራ ፑርዲ (Laura Purdy)፣ የላየልስ-ክራውች ትራድሽናል አካዳሚ (Lyles-Crouch Traditional Academy) - (Lyles-Crouch) የካፊቴሪያ የምግብ አገልግሎት ማናጀር፤ ከACPS ጋር፣ ከ2015 ጀምሮ የነበሩ።
- ማሪኦ ያች (Mario Yach)፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት (, Alexandria City High School (ACHS) - ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) የህንፃ መሃንዲስ፤ ከACHS እና ከACPS ጋር ከ2006 ጀምሮ የነበሩ።

የACPS - ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) - ያልተጠበቀ ጉብኝት በማድረግ ለ'VIP' ሽልማት ተቀባዮቹ - በስራ-ቦታቸው ላይ እያሉ- እና ሐሙስ ኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 - የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ላይ - ለሕዝብ-ይፋ ሆኖ እውቅና-ባገኙበት በግል-ተጋብዘዋል። እያንዳንዱ የሽልማቱ ተሸላሚዎች፤ ልዩ-የሆነ የACPS የስጦታ-ቦርሳን እና የ'VIP' ሰርተፊኬትን አግኝተዋል።

"ሚስ ባልድዊን (Ms. Baldwin)፣ ይህ የ'VIP' ሽልማት - በልዩ የመጓጓዣ አገልግሎት ልቅነታቸው የሚገባቸው ነው፤ ያላቸው ደግ-ልቦና በስራቸው ያስታውቃል፣ እና ሁሉንም ተማሪዎችን በየቀኑ በማጓጓዝ ያላቸውን-ድንቅ እንክብካቤ ያሳያል፤" ብለዋል ኪምበርሊ ካርል (Kimberly Carll) - የACPS የግል ምደባ ባለሞያ። እርሳቸውም እንዳሉት፤ ባልድዊን (Baldwin) ደከመኝ-ሳይሉ - በግል የተመደቡ ተማሪዎች መጓጓዣን በደህንነት-ተጠብቆ እንዲያገኙ እና በጊዜው ወደየትምህርት ቤቶቻቸው መድረሳቸውን ያረጋግጣሉ። "በማንኛውም ጊዜ ልዩ የሆነ አስቸጋሪ-ሁኔታ በሚገጥመን ጊዜ፤ ተማሪ-ተኮር ሆነው-መፍትሄውን ፍለጋ ላይ እንስራ-ይላሉ፤" ካርል (Carll) ጨምረውበታል፤ ባልድዊን (Baldwin) - ከቤተሰቦች ጋር አጋርነትን በቡድን ሆኖ በመፍጠር፣ ለችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ-ጊዜያቸውን ይሰጣሉ።

እንደ ላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) የካፊቴሪያ የምግብ አገልግሎት ማናጀርነት፤ ፑርዲ (Purdy) - ሁሉም ተማሪ የሚፈልጉትን ዓይነት ተመራጭ የሆነ የምሣ መመገብ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ከሚያደርጉት ውስጥ ጎልተው-የሚታዩ ናቸው። "ለላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) እና ለማህበረሰቡ የሚያሳዩትን ምሳሌያዊ ስለሆነው አገልግሎታቸው እና ፍቅራቸው፣ እናመሰግናለን፤" ብለዋል የላየልስ-ክራውች (Lyles-Crouch) - የ'PTA' ፕሬዚዳንት፣ ማቲአስ ፓአላቬቺኖ (Matias Palavecino)። በማስታወስም-ሲናገሩ፤ ፕሩዲ (Purdy) በዓመታት ውስጥ በርካታ ሽልማቶችን ያገኙ ሲሆን በቅርብ-ጊዜ እውቅናን ያገኙበት በስቴት-ደረጃ - በNo Kid Hungry School Lunch Heroes Virginia Hall of Fame ላይ ክብርን-ያገኙበት ነበር። የትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች (School Nutrition Services) ዳይሬክተር፤ የሆኑት ሲንቲያ ሆርሜል (Cynthia Hormel) ጨምረው-ሲናገሩ፤ "ሎራ (Laura) ጥሩ የሆነ የአመራርነት ችሎታዎች ያላት፣ እና ጥሩ ማናጀር እንደሚወጣት፣" ቀድሞውኑ አውቀውት-እንደነበር ተናግረዋል።

በACHS ውስጥ - "ዋጋው-ሊተመን የማይችል/invaluable" ተቀጣሪ-ሠራተኛ ተብለው የተጠሩት፤ ሁልጊዜ ስራውን ለማስፈጸም መንገድ የማያጡት - ያች (Yach) - እንደ የህንፃ ኢንጂነር ሆነው - የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ፣ የሠራተኛ እና የተማሪን ፍላጎቶች እንዲያሟላ ሆኖ ክንውኑን ማካሄዱን ለማረጋገጥ - ከሚገባው-በላይ እውቀት-ያላቸው እና ከሚችሉት በላይ ጥረት-እያደረጉ የሚሰሩ፣ ምስጋና-የሚቀርብላቸው ናቸው። "የሚቀያየረውን የአየር-ጠባይ ወቅትን በመጠበቅ - ሁሉም HVAC መስራታቸው በማረጋገጥም-ሆነ፤ ተማሪዎች ቦታዎቻቸውን እንዲያገኙ በሚሰቀሉ አዲስ-ምልክቶችም ወይም በህንፃው ዙሪያ የራሳቸውን የማጠናቀቂያ አሻላራችውን በሚጥሉበት ነገሮች ላይ ሁሉ፤ ሚ/ር ማሪኦ (Mr. Mario) ሁልጊዜ ከፈገግታ-ጋር ሁሉንም ለመርዳት የሚችሉ እና ፈቃደኛ-የሆኑ ናቸው፤" ብለዋል የACHS - ኪንግ ስትሪት - ተጠባባቂ የካምፓስ አስተዳዳሪ - ክርስተፈር ስፒኢች (Christopher Speich)።

# ኖቬምበር (Nov.) 14 ቀን 2022፤ የትምህርት ቤት ቦርድ የ‘Public Hearing’ - ሃሳብ-በቀረበበት የACPS ‘CIP’ በጀት ላይ




የትምህርት ቤቱ ቦርዱ፤  ሰኞ፣ ኖቬምበር (Nov.) 14 ቀን 2022፣ በ6:30 p.m. ላይ የ‘FY 2024-33 CIP Budget’ን በኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ላይ የቀረበውን - የ‘Public Hearing’ን አዘጋጅቷል። የ‘CIP’ በጀት፤ የገንዘብ እርዳታውን ለThe High School Project፣ የሦስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘመናዊነት-ስራ፣ አዲስ-ትምህርት ቤትን በግንባታው-ጊዜ እንደ ተለዋዋጭ-ቦታ ሆኖ ጥቅም-ላይ ሊውል የሚችል የአዲስ ትምህርት ቤትን መጠቀም፣ ተጨማሪ-የሆኑ - በCIP እና የዘመናዊነት ስራው ጊዜ ወቅት - ለመጓጓዣ-ተቋም በዚህ-ዓመታት ውስጥ፤ የሚያቀርብ-ይሆናል።

በ‘CIP’ በጀት ላይ ንግግር-ማድረግ ፍላጎት ያላቸው ከሕዝብ-የተውጣጡ አባላቶች፤ በአካል-ተገኝቶ፣ በዙም (Zoom) ወይም የጽሁፍ የሕዝብ አስተያየቶችን በthe online form አማካኝነት-ለማቅረብ ሊመዘገቡ (sign up ሊያደርጉ) ይችላሉ። ከ‘CIP’ በጀት ጋር ተያያዥ-የሆኑ አስተያየቶች ብቻ የሚሰሙ-ይሆናል። መመዝገቢያው የሚያበቃው - ከ ‘public hearing’ ከሚድረግበት - ከእሁድ፣ ኖቬምበር (Nov.) 13 ቀን 2022 - አንድ-ቀን በፊት ከቀትር-በፊት ይሆናል።

የ‘CIP’ በጀት የስራ ክፍል አንድ (Work Session One)  - ከተጠራው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ወዲያውኑ-ተከትሎ የሚካሄድ ይሆናል። በተቀጣሪ-ሠራተኛ ማካካሻዎች (Employee Compensation) ለFY 2024 Combined Funds (CF) በጀት ላይ፤ የሚቀርብ (presentation) የሚኖር-ይሆናል።

በልዩ-ሁኔታ የተጠራውን ስብሰባ ለመመልከት ወይም የበጀት የስራ ክፍል (Work Session) በዙም (Zoom) አማካኝነት ለመከታተል፤ እባካችሁ በዙም (Zoom) አማካኝነት፣ ተቀላቀሉ ወይም በትምህርት ቤት ቦርድ ድህረ-ገጽ ላይ ተመልከቱ።

**የACPS - ተቋማት እና ክንውኖች (Facilities and Operations) መምሪያ፤ እንደ የተማሪ መጓጓዣ እና ተንቀሳቃሽ-መኪናዎች ቁጥጥር (Pupil Transportation and Fleet Management) - ዳይሬክተር አድርጎ - ሚቻሌ ጆንሰን (MeChale' Johnson)ን፣ እንኳን-ደህና መጡ ብሏል**



ሚቻሌ ጆንሰን (MeChale' Johnson)፤ ወደ አሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - እንደ አዲስ የተማሪ መጓጓዣ እና ተንቀሳቃሽ-መኪናዎች ቁጥጥር (Pupil Transportation and Fleet Management) - አዲስ ዳይሬክተር ሆነው ተቀላቅለዋል። ጆንሰን (Johnson)፤ እንደ የመጓጓዣ ዳይሬክተር ሆነው ከፎልስ-ቸርች ከተማ የሕዝብ ትምህርብ ቤቶች (Falls Church City Public Schools) ውስጥ - ካገለገሉ በኋላ፣ ከACPS ጋር - አዲሱን የስራ-ድርሻቸውን ተቀብለዋል። ከዚህ-ቀደም፣ በመጓጓዣ ክፍሎች ውስጥ በሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ (University of Maryland (UMD)፣ በ'Southeastrans Inc.'፣ እና በዋሽንግተን አካባቢ የትራንዚት ባለሥልጣን (Washington Metropolitan Area Transit Authority (WMATA) ጋር፤ በተለያዩ የበላይ-ተቆጣጣሪነት የስራ-ድራሻውል ይዘው-አገልግለው-ነበር። በ'WMATA' ውስጥ፤ ጆንሰን (Johnson) - እንደ የአውቶቡስ ስምሪት ማናጀር፣ የስልጠና ማናጀር፣ እና የአውቶቡስ መንገድ የስክምሪት-ክንውን - ረዳት ጠቃላይ-ስራ አስኪያጅ ሆነው አገልግለዋል።

ጆንሰን (Johnson)፤ የባችለር ዲግሪን - ከ'UMD' በወንጀል-ጥናት (criminology) እና በወንጀል ፍትህ (criminal justice) - እንዲሁም የማስተርስ-ዲግሪያቸውን በቢዝነስ-አድሚኒስትሬሽን አግኝተዋል። ጆንሰን (Johnson)፣ የተመደቡበትን የስራ-ድርሻ፣ ኖቬምበር (Nov.) 14 ቀን 2022 ይጀምራሉ።

"ሚ/ስ ጆንሰን (Ms. Johnson) ወደ ተቋማት እና ክንውኖች ቡድናችን (facilities and operations team) - እንደ የተማሪ መጓጓዣ እና ተንቀሳቃሽ-መኪናዎች ቁጥጥር (Pupil Transportation and Fleet Management) - አዲስ ዳይሬክተር ሆነው እንኳን-ደህና መጡ-ስል ደስታ ይሰማኛል፤" ብለዋል ዶ/ር አሊሲያ ሃርት (Dr. Alicia Hart) - የACPS የተቋማት እና ክንውኖች ሹም (Facilities and Operations Chief)። "ለዚህ የስራ-ድርሻ - ልዩ የሆነ የችሎታ-ጥምረትን ይዘው ያመጣሉ፣ እና በደንበኛ አገልግሎት፣ በባለድርሻ-አባል እገዛ፣ እና ለተማሪ የመጓጓዣ አገልግሎቶች የፈጠራ አቅጣጫን በመፍጠር ትኩረት ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ።"

## የACPS - ተቋማት እና ክንውኖች (Facilities and Operations) መምሪያ፤ እንደ ካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ እና ዲዛይን አዲስ ዳይሬክተር አድርጎ - አዝጃርጋል “አዙካ” ባርትሌት (Azjargal “Azuka” Bartlett)ን አስተዋውቋል



አዝሃርጋክ “አዙካ” ባርትሌት (Azjargal “Azuka” Bartlett)፤ በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፣ እንደ የካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ እና ዲዛይን ዳይሬክተው ሆነው - አዲስ የስራ-ድርሻቸውን ወስደዋል። ከዚህ-ቀደም እንደ ሲኒየር የካፒታል ፕሮግራም ማናጀር ሆነው በACPS ውስጥ ያገለግሉ ነበር። ለክፍሉ/division፤ ባርትለት (Bartlett) እንደ - የግንባታ ፕሮግራም ማናጀር ሆነውም-አገልግለዋል። ወደ ACPS ከመምጣታቸው አስቀድሞ፤ ባርትለት (Bartlett) - እንደ አርክቴክቸራል ዲዛይነር ሆነው - ከአርክቴክቸራል ዲዛይን ስቱዱዮ (Architectural Design Studio) ጋር ሰርተዋል።

ባርትሌት (Bartlett) - የባችለር ዲግሪያቸውን በኢንቲሪየር ዲዛይን (interior design) - ከኮርኮራን (Corcoran) የአርትስ እና ዲዛይን ትምህርት ቤት ያገኙ፤ እንዲሁም፣ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በሪል-ስቴት ግንባታ እና የገንዘብ-አያያዝ (real estate development and finance) ከጆርጅታውን ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። ባርትሌት (Bartlett) ወደ አዲሱ የስራ-ድራሻቸው፣ ከኦክቶበር (Oct.) 31 ቀን 2022 ጀምሮ-ተዘዋወረዋል።

“ሚ/ስ ባርትሌት (Ms. Bartlett) - የላቀ-ደረጃ ያለውን የአመራርነት ብቃታቸውን በፕሮጀክት ማናጅመንት - በፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት ላይ ያሳዩ ሲሆን፤ ይህም ተከፍቶ የነበረው በ2018 ላይ የነበረ እና፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮጀክትን - ከጃንዋሪ (January) 2021 ጀምሮ - ለACPS ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር ሲያስተዳድሩ-ቆይተዋል።  አዲስ የትምህርት ቤት ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም  እና ለክፍሉ/division የካፒታል ዕቅድ-አወጣጥ ጥረቶችን ለመምራት፣ የሚጠይቀውን ይህን የስራ-ድርሻ ስለወሰዱ - ደስታ ተሰምቶኛል፤” ብለዋል የACPS የተቋማት ዋና ዳይሬክተር - ኤሪካ ጉሊክ (Erika Gulick)።

# ለአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ-አጠቃቀም፤ እርዳታን-ማግኘት: እንቅፋት ሊኖን የሚችለውን - መገለል (Stigma)ን ለመቅረፍ-ምላሽ መስጠት

SUBSTANCE ABUSE PREVENTION COALITION OF ALEXANDRIA

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ላይ ምላሽ-መስጠቱን የቀጠለ እና፤ ይህም፣ ማህበረሰቡን በአጠቃላይ-ላይ እና በትምህርት ቤቶች ላይ - እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያደር፣ እና የመረጃ-ምንጮችን ለማህበረሰባችንን በማጋራት የሚቀጥል-ይሆናል። በዚህ ዣምንት፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ከአደንዛዥ-ዕፅ ጋር በተያያዘ እርዳታን-ከማግኘት ሊከለክላቸው ከሚችለው - በ'መገለል (stigma)' ላይ የቅርብ-ትኩረት የምንሰጠው-ይሆናል። በተጨማሪም፤ ለቤተሰቦች ተጨማሪ ግሩም የሆነ የመገኛ-ምንጭ ሊሆንላቸው ከሚችለው የ[አሌክሳንድርያ - አደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition)](#) ውስጥ ከሚሰሩት ከስራ-ባልደረቦቻችን ጋር በመሆን በቅርበት-እንሰራለን።

ማግለል (Stigma)፤ ዕጾችን የሚጠቀሙ ግለሰቦችን እና በዚህም-ምክንያት ሱሰኛነትን የሚያዳብሩትን - በማግለል አድልዎን የመፍጠር-ዓይነት ነው። ልጆች እና ወጣቶች - ዕፆችን በተለያየ ምክንያቶች ይጠቀማሉ፤ እና ማግለል (Stigma) - የተለያዩ ምክንያቶችን እንደ የአዕምሮ ጤና ማስፈለግን፣ ቀውስ (trauma)፣ የቤተሰብ ግጭቶች ወይም ከእኩዮቻቸው በሚደርስ ተጽዕኖ እና በአካባቢያዊ ምክንያቶች፤ ሳቢያ - ዕጽን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ካለመረዳት ጋር የተያያዘ ነው። ማግለል (Stigma)፤ በተጨማሪም ስለ - በዕፆች ውስጥ ያሉ ቶክሲኖች እንዴት ቀስ-እያለ ወደሚመጣ የአዕምሮ እድገት-መግታት እንደሚዳርግ፣ ለረጅም ጊዜ በተደጋጋሚ ዕፅን መጠቀም መጨመር እና የማማር-ሁኔታ ማሳየት መጀመር፣ እና አዕምሮ በእነዚህ አደንዛዥ ዕፆችን በመጠቀም-በእነሱ ላይ የማንዘንበል ሁኔታን በማሳየት-ሊፈጥሩ የሚችሉ ችግሮችን ካለመረዳት ጋር የተያያዘም-ነው። በተጨማሪም - ሌላው የማግለል (stigma) ዓይነት፤ ስለ ሱስ፣ ህክምና እና ከዚህ-የመውጣት ሂደት ስራ ላይ በሚኖር-ውሱን ከሆነ ግንዛቤ ጋር በተያያዘም-ነው። የACPS የአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም አገልግሎቶች - ዒላማ አድርጎ  ማግለል (stigma)ን ለማስከተል የሚችሉትን፣ እነዚህን ምክንያቶች - ትምህርትን በመስጠት እና የቅድመ ጣልቃ-ገብነት መረጃዎችን - ስለ ዕፅ መጠቀም ባህሪያቶች - ለልጆች እና ቤተሰቦቻቸው እነዚህን ችግሮች እንዲረዱ እና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

በACPS ውስጥ፤ ከእነዚህ የአደንዛዥ-ዕፅ አጠቃቀም ጋር እየተቸገሩ ያሉት ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፤ ወደ  [Department of Student Services and Equity (DSSE) for support and assistance](#) እርዳታን-እንዲጠይቁ፤ ያበረታታል።  ተማሪዎቻችንን እና ቤተሰቦችን በዚህ-ጉዳይ ላይ እንዲረዱ፤ በአደንዛዥ-ዕፅ - ስልጠና ያላቸው ባለሞያዎች - አለን። በችግሩ ላይ ስያሜ በመስጠት - እርዳታ-ለሚጠይቁት ሰዎች - ወደ ማግለል (stigma) ሊመራ የሚችል ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን - እርዳታው - እንክብካቤ የተሞላበት እና ስሜታዊነትን ስለሆነ - ማግለሉ እውን-ሊሆን አይችልም። ስለ አደንዛዥ-ዕፅ መጠቀም - በምንናገርበት ጊዜ - የ[ጆን ሃፐኪንስ ህክምና (Johns Hopkins Medicine)](#) (JHM) እንደሚገልጸው፤ ማጣጣልን ወይም ከግምት-ውስጥ አስገብቶ ፍርድ-የመፍረድ አባባሎችን የሚያስተናግዱት መጠቀም፤ እንደ -  “በምናገለግለው-ማህበረሰባችን ውስጥ፣ አስቸጋሪ ከሆነ ሱስ እና በከፍተኛ-ሁኔታ ከመጠቀም (overdose) ለመውጣት ዋነኛ-የሆነ መሰናክል ነው።” የ[National Institute on Drug Abuse](#) (NIDA)፤ ማግለል (stigma)ን በአደንዛዥ-ዕፅ አጠቃቀም ክሎች ዙሪያ ለማስወገድ -  እና ከሱሰኝነት ጋር የሚገኙ ሰዎችም-ለበሽታቸው ተወቃሽ ሆነው የሚቀጥሉበትን ሁኔታ በማስቀረት ዙሪያ - ብዙ መሥራት እንዳለበት-አውቋል። ‘NIDA’ እንዳለው-ከሆነ፤ ሕክምና-እንደደረሰበት - ሱሰኝነት፣ “ውስብስብ

የሆነ የአዕምሮ እክል ሆኖ - ከባህሪያዊ ይዘት-ጋር አብሮ የሚመጣ" መሆኑን የሚስማማበት-ሲሆን፤ በርካታ ሰዎች አሁንም-ቢሆን ግን፣ እንደ የሞራል-ድክመት እና ትክክል-ያልሆነ ባህሪይ ከመሆን የሚመጣ አድርገው ይመለከቱታል።

በACPS ውስጥ፣ 'DSSE' አካትቶ የሚሰራው - የMulti-Tiered System of Supports (MTSS) approach በውስጡ ያካተታቸውን - የቅድመ እና የላቀ-ደረጃ ያለው የጣልቃ-ገብነት አገልግሎቶችን - አንድ ተማሪ ከአደንዛዥ-ዕፅ ጋር ተሳታፊ-ሆኖ ለእኛ-በሚነገረን ጊዜ፤ እንዲሁም - ከአደንዛዥ-ዕፅ ጋር ተሳታፊ-ከሆን ጋር አብሮ-የሚመጣ አደገኛ-የሆነ ሁኔታዎችን፣ ተማሪዎችን ለማስተማር እና ግንዛቤ-እንዲኖራቸው የማደርግ አጠቃላይ የሆነ የመከላከያ አገልግሎቶችን መስጠትን-ያካትታል። ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አጋዥ-የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ፤ ለሁሉም ተማሪዎቻችን በጣም-ጠቃሚ ነው። ከቤተሰቦች ጋር - እነርሱን ለማስተር እና የመረጃ-ምንጮች (resources) እና መረጃዎችን - እንደወላጅነት እና እንደአሳዳጊነት፣ ይህ ተቀዳሚ ኃላፊነታቸው ስለሆነ፣ ለተማሪዎች እርዳታን ለማግኘት ቤተሰቦችን እንዲረዳ - ከቤተሰቦቻችን ጋር አጋርነትን ፈጥረናል።

'DSSE' እገዛ-የሚያደርገው፤ በመከላከል እና በቅድመ ጣልቃ-ገብነት ፕሮግራሞች (prevention and early intervention programs) ላይ፣ እንደየ-ግለሰቡ ሁኔታ ፍላጎቶቹ ሊያያዩ የሚችሉትን በመከተል-ነው። እነዚህ እርዳታዎች የሚያካቱት ፕሮግራሞች፤ ተማሪዎች ሕገ-ወጥ ዕፆች እና አልኮል-መጠጦች ስላላቸው ጉዳት እና፣ ዕፆችን እና ለሌሎች አደንዛዥ-ዕፆችን ከአለአግባብ-በመጠቀም ስለሚመጡ ጉዳቶች ማስተማርን-ያካትታል። የሠራተኞች ፕሮግራሞችም፤ አደንዛዥ-ዕፅን አጠቃቀም ወደ መለየት፣ እንዲሁም ወደ አንደኛው ከአለአግባብ-መጠቀም ባለሙያተሞች - ጣልቃ-ገብነት ሊያስፈልግው የሚችለውን እነዚህን ተማሪዎች እንዴት-መምራት (referral ማድረግ) እንደሚቻል የሚመራቸው-ይሆናል። የአደንዛዥ-ዕጽ አለአግባብ አጠቃቀም መከላከያ እና የቅድመ-ጣልቃ ገብነቶች መምሪያዎች - የቡድን ተሞክሮችን፣ የየግል የማማከር አገልግሎትን እና ግመገማን፣ እና ሌላ ፕሮግራሞችን ማቅረብ-ይችላሉ። በተጨማሪም፤ መመራቶች (referrals) ለተማሪዎች እና ለወላጆች - ወደ ማህበረሰብ ድርጅቶች እርዳታን ለማግኘት - በወላጆች ወጪ- ለመመራት ይቻላል።

በትምህርት ቤታችን ውስጥ፣ ሕገወጥ የሆኑ ዕፆችን መያዥ ለተማሪዎች ደህንነትን-ያልጠበቀ ነው። ይህን ጉዳይ መፍትሄ-ለመስጠት፤ ACPS ፖሊሲዎች እና ደንቦች አሉት። የACPS ፖሊሲዎች እና ደንቦች (policies and regulations) ተማሪዎች - ማንኛውንም አልኮል፣ ትንባሆ፣ እና/ወይ የትንባሆ ምርቶችን ወይም ሌላ ዕፆችን በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ውስጥ፣ ወይም በትምህርት እንቅስቃሴ ወቅት፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም ውጪ፤ መያዝ፣ መጠቀም እና/ወይም ማከፋፈል እንደማይችሉ፤ በግዳጅነት-አስቀምጧል። ይህ የሚያካትተው፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ጭስ-አልባ ትንባሆ፣ ኢ-ሲጋራዎች፣ አናቦሊክ ስቴሮይዶች (anabolic steroids)፣ ዕፆችን የሚመስሉ (look-alike drugs)፣ የዕፅ ፓራፈርኔሊያ (drug paraphernalia) እና ማንኛውንም በሃኪም-ትዕዛዝ ወይም ትዕዛዝ የሌላቸው ዕፆችን (prescription or non-prescription drugs) - ከዚህ ፖሊሲ ጋር በሚከበር-ሁኔታ መያዝ-ወይም መጠቀምን ይከለክላል።

ፖሊሳችንን ከመከተል - ጋር አብሮ በሚሄድ ሁኔታ፤ ACPS - ከአደንዛዥ-ዕፅ ጋር በመሆን ተቸግረው-እየታገሉ ያሉትን ተማሪዎቻችንን ፍላጎቶች-ለማሟላት የወደ-መልካም-ቦታ የሚመልስ አቀራረብ (a restorative approach)ንም አካትቶ-ይወስዳል። እነዚህ የተሟሯቸው ባህሪያቶች፤ በአጠቅላይ ባህሪያቸው በትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ ተማሪዎቻችን ለመግለጽ እና ለመረዳት እንዲችሉ በመርዳት፤ ምላሽ-የሚሰጥበት ይሆናል። ለምሳሌ፤ ተማሪው ለመጀመሪያ-ጊዜ ላደረገው ጥፋት-ተማሪው እንዲታገድ (suspend የተደረገ) ከሆነ፤ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ሊሳተፉበት የሚችሉት ሴሚናር አለ። ለተጨማሪ መረጃ፤ እባካችሁ የACPS የተማሪ የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct)ን እባካችሁ ተመልከቱ።

ትምህርት ቤታችንን እና ተማሪዎቻችንን በደህንነት ስለመጠበቅ - ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የሚያስፈልጓቸውን ጠቃሚ መረጃዎችን በማግኘት-እንዲቀጥሉ፤ ACPS - ምላሽ-ሰጪ በመሆን እና በንቃት በመስራት የሚቀጥል-ይሆናል። የACPS 'Substance Abuse Prevention & Educational Intervention' ድህረ-ገጽ፤ መረጃዎችን እና የመረጃ-ምንጮችን የሚያቀርብ ሲሆን፤ በፈተኖል (fentanyl) ለወጣት እና አዋቂዎች የሚሰጠውን 'fact sheets'ን አካትቶ፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ማግኘት-ይቻላል።

# ወደ ‘ቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) 2022 - የፖስተር ውድድር ውስጥ ለመግባት የመጨረሻ-ዕድል




ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች በሙሉ፣ ከዕፅ-ነፃ የሆነ የአኗኗር-ዘዴን ለማበረታታት እንዲረዳ፣ በቀይ-ሪባን የፖስተር ውድድር (2022 Red Ribbon poster contest) ውስጥ ስራዎቻቸውን እንዲያስገቡ ይበረታታሉ። የዚህ ዓመት መለያ-ገጽታ (theme)፣ “Celebrate Life: Live Drug Free.” ነው።

ሦስት የማስገቢያ ምድቦች አሉት: የመጀመሪያ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። ሁሉም ፖስተሮች፤ እስከ ኖቬምበር (Nov.) 15 ቀን 2022 ድረስ - ፖስታ-የተላከበት ምልክት እንዲኖራቸው እና እንዲገቡ ያስፈልጋል:

ሚስ ዳኒኤላ ፔሬዝ-ብራቮ (Ms. Daniela Perez-Bravo)
ACPS Central Office at
1340 Braddock Pl, 5th Floor,
Alexandria, VA 22214

የኤሌክትሮኒክ ስሪቶቹ (Electronic versions)፤ ወደ face@acps.k12.va.us ወይም በwww.acps.cc/RRWposter22 ሊገቡ-ይችላሉ።.

ከዕፅ-ነፃ የሆነ የአኗኗር-ዘዴን የሚያበረታታ፤ በሰዓሊነት አቀራረብ እና በጠንካራ መልዕክት አቀራረባቸው ላይ መሠረት አድርጎ፤ ሦስት አሸናፊ የሆኑ ፖስተሮች ይመረጣሉ። የ‘Red Ribbon poster’ ውድድር አሸናፊዎች፤ እያንዳንዳቸው የ$100 የስጦታ ካርድ (gift card) የሚያገኙ፣ እና የሰሩትም ፖስተር - በ2023 የቀይ-ሪባን ሣምንት 2023 (Red Ribbon Week 2023) ወቅት-ውስጥ እንዲታይላቸው ይደረጋል።

የ‘ቀይ-ሪባን ዘመቻ (The Red Ribbon campaign)’፤ በሃገሩ ውስጥ ለረጅም-ጊዜያት ሲያገለግል የነበረ እና ትልቁ የዕፅ መከላከያ ፕሮግራም ነው። የACPS፣ የ‘FACE’ ማዕከል - ይህን ዘመቻ ወደ አሌክሳንድርያ በዚህ በልግ (fall) - ከአሌክሳንድርያ አደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ መጠቀም መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandria)፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (City of Alexandria’s Department of Community and Human Services)፣ (Stop Child Abuse Now of Northern Virginia) እና ማንጓጠጥን ጨርሶ-ለማጥፋት የከንቲባ ዘመቻ (Mayor’s Campaign to End Bullying) ጋር አጋርነትን-ፈጥሮ ተመልሶ-መምጣቱን በደስታ-ይገልፃል።

የ‘ቀይ-ሪባን ዘመቻ (The Red Ribbon campaign)’፤ ወደ ‘Celebrate Life. Live Drug Free.™ - በብልጽግና-እየተጓዘን ባለንበት ጊዜ፤ ስለእነርሱ-ብቻ ከማውራት ይልቅ፣ ከወጣቶች፣ ጋር ግንኙነት በማድረግ - አብሮ-በአንድነት ለመቆም እና በጉልህ-በሚታይ ሁኔታ - ዕፆችን በመቃወም በመቆም ማሳየት የሚቻልበት-ውጤታማ የሆነ መንገድ ነው።

# ወደ ነፃ ክትባት፣ የጤና እና የደህንነት-ጥበቃ ትዕይንት - ኖቬምበር (Nov.) 12 ቀን 2022 ላይ እንድትገኙ፣ ተጋብዛችኋል




የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የ"Time to Boost" - ነፃ ክትባት፣ የጤና እና የደህንነት-ጥበቃ ትዕይንትን - ለሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ቅዳሜ፣ ኖቬምበር (Nov.) 12 ቀን 2022 - ከ9:30 a.m. እስከ 1:30 p.m. ድረስ፣ በዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (5700 Sanger Ave) ውስጥ ያካሂዳል።

ለዚህ ዝግጅት-የቀረቡት ዝርዝሮች፣ እንደሚከተለው-ቀርበዋል:

- ካለ-ቀጠሮ (Walk-in) የCOVID-19 ክትባት - ዕድሜያቸው አምስት-ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ - ለሁሉም-ሰው የሚሰጥ-ይሆናል።
- የሜዲኬድ (Medicaid) ምዝገባ እና ምእረጃዎች - የሚዲካል እና የጥርስ ህክምና አቅራቢዎችን ማግኘትን-ጨምሮ- መረጃዎች ይኖራሉ።
- የክፍሉ/Division - ቤተሰቦች - ከትምህርት ቤት ነርስ ጋር የመነጋገር ዕድል አግኝተው-ጥቅም እንዲያገኙ እና በዝግጅቱ ላይ ከሚታዩት የጤና እና የጤናማነት ትዕይንቶች ትምህርት-እንዲያገኙ፤ ተጋብዘዋል።
- ነፃ ከሆኑ መጽሐፍቶች ጋር-ታሪክን የማንበቢያ ጊዜ፣ የእሳት-አደጋ መምሪያ እና ፖሊስ - 'Touch-a-Truck'፣ ምግብ እና ሽልማቶችም - የሚኖሩ-ይሆናል።

መረጃው፤ በዝግጅቱ የቀን-መቁጠሪያ ዝርዝር (event's calendar listing) ላይ የሚገኝ-ሲሆን፤ የመወሰጃ (pick-up) እና የማውረጃ (drop-off) ጊዜያቶች፤ ከኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት፤ ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂ፤ ጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት፣ አሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)፣ እና ሳሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker) የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት - ለነፃ የአውቶቡስ ሻትል (bus shuttle) ያካተተ-ነው።

## የኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ



በዚህ ኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 ስብሰባው ላይ፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ርዕሶች ላይ ተነጋግሮበታል:

- የ2022-23 የ'Vision Integrity & Passion (VIP)' ሽልማቶች - የመጀመሪያ-ተቀባዮችን ዕውቅና-መስጠት።
- የአባልነት እና የመሸጋገር ሪፖርት።
- በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) ላይ አዲስና-ማሻሻያ (Update)።
- ለFY 2024-2033 የ'CIP' በጀት - አቀራረብ (Presentation)።
- የፕሮግራም ጥናቶች።
- የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) እና የአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ - የመተዳደሪያ ደንብ (Memorandum of Understanding (MOU)ን - ማራዘም።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘትም ትችላላችሁ።

## በኖቬምበር (Nov.) 3 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ኖቬምበር (Nov.) 3 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 86.56 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኖቬምበር (Nov.) 3 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።